# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 347 ታህሳስ 24 2007


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

የሀገሪቱ ብሄራዊ ባንክ ንብረት የሆ ነው ወርቅ በባሌስትራ ለውጦ እስከ መዝረፍ የደረሰ በጠራራ ፀሀይ የህ ዝብና የሀገር ሀብት ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ በጥቂቶች የሚዘረፍበት ዘመን ቢኖር የምንገኝበት ዘመን ወያኔ ብቻ ነው። የጅምላ እስር፤ የጅምላ ግድያ፤ የጅምላ ስደትና መፈናቀል፤ ይበልጡንም በታሪካችን ታይቶ በማያውቅ መልኩ ለሞት፤ ለእስር፤ ለመፈናቀልና ለስደ ት ምክንያቱ የተገኘንበት ዘውግ የሆነበት ዘረኛ ዘመን ቢኖር ይኸው ዘመነ ወያኔ ብቻ ነው።

ግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## አራት ከፍተኛ ማዕረግ ያላቸዉ ተዋጊ ጀት አብራሪ የአየር ኃይል መኮንኖች ወያኔን አናገለግልም ብለዉ ኬንያ ገቡ

የወያኔ ዘረኝነት ያንገበገባቸዉና የወገናቸዉ መረገጥ፤ መታሰርና በግፍ መገደል ያንገፈገፋቸዉ አራት የኢትዮጵያ አየር ኃይል ተዋጊ ጀት አብራሪዎች ከአሁን በኋላ ወገናችንንና አገራችንን ነዉ እንጂ ዘረኝነትን አናገለግልም ብለዉ ኬንያ መግባታቸዉን የኢትዮጵያ ሳቴላይት ቴሌቪዥን ባለፈዉ ረቡዕ ዘገበ። ምድብ የበረራ ጣቢያቸዉ ድሬደዋ የነበረዉ እነዚህ አራት ከፍተኛ የአየር ኃይል መኮንኖች በአየር ኃይሉ ዉስጥ ከፍተኛ ልምድና የዉጊያ ችሎታ ያካበቱ ከመሆናቸዉም በላይ አየር ኃይሉን ለረጅም አመታት ማገልገላቸዉ ታዉቋል። የወያኔ አፈና፤ ድብደባና ግድያ በከፍተኛ መጥን እየጨመረ በሄደባቸዉ ባለፉት ሁለት አመታት ዉስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ወያኔን እየጀዱ የነጻነት ኃይሎችን በመቀላቀል ላይ መሆናቸዉ የሚታወቅ ሲሆን በተለይ ከሰሞኑ ባገባደድነዉ የፈረንጆቹ አመት ወያኔ በተያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የፈጸመዉ ግድያና እስር ለብዙ የመከላከያ ሠሽራዊት አባላት መኮብለል ምክንያት ሆኗል።

ይህ ከሰሞኑ ወያኔን ከድተዉ ኬንያ የገቡት የአየር ኃይል አባላት ዜና የተሰማዉ ወያኔ አንድ ተዋጊ ሂሊኮፕተር አስገድደዉ ኤርትራ ያሳረፉትን ፓይለትን የበረራ መሀንዲስ አስመልክቶ አየር ኃይሉን ማመስ በጀመረበት ማግስት በመሆኑ ዜናዉ በወያኔና በደጋፊዎቹ ዉስጥ ከፍተኛ ድንጋጤ መፍጠሩን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸዉ ወገኖች ተናግረዋል። አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ ታማኝ ዉስጥ አዋቂ ምንጪች እንደሚናገሩት ከሆነ ወያኔ ካሁን በኋላ በቅርብ ከሚያዉቃቸዉና ከሚያምናቸዉ ዉጭ ሌሎች ፓይለቶችን ለበረራ ልምምድም ቢሆን አምኖ እንደማይልካቸዉ ለማዉቅ ተችሏል። ባሳለፍነዉ ሳምንት አራቱ ከፍተኛ የአየር ኃይል መኮንኖች ከጠፉ በኋላ ወያኔ የነሱን፤ የጓደኞቻቸዉንና የዘመመዶቻቸዉን ቤት እየፈተሸ መሆኑንኑ ምንጮቻችን አክለዉ የላኩልን ዜና ያስረዳል።

## ህወሓት የ40 ኛ አመት የዘረኝነት በዓሉን ለማክበር ከ 150 ሚሊዮን ብር በላይ የአገር ሐብት አወደመ

ዘረኛው የሕወሓት አገዛዝ ከሰሞኑ ታላቋን ትግራይ ለመመስረት በማቀድ ደደቢት በረሐ የከተቱበትን 40 ኛ አመት ለማክበር በሚል የአገዛዙ ቱባ ሹማምንቶች፣ ታዋቂ የአገሪቱ አርቲስቶች እንዲሁም ጋዜጠኞችን በአገዛዙ ሙሉ ስፖንሰርነት ድርጅቱ የተመሠረተበትንና የትጥቅ ትግል የተካሄዱበትን ቦታዎች ለማስጎብኘት በሚል ከ150 ሚሊዮን ብር በላይ የአገር ሐብት መውደሙን የውስጥ ምንጮቻችን አመልክተዋል። በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ የተተፋው ዘረኛው የህወሓት አገዛዝ ዝግጅቱን ለማዘጋጀት ያነሳሳው በተለይ በህዝብ ዘንድ ተወዳጅና ታዋቂ ናቸው ተብሎ የታሰቡትን አርቲስቶችንና ሌሎቹንም ተጋባዥ እንግዶች ከህዝብ ጋር እንዲያስታርቁት ለመማጸንና የዘረኛውንና ነፍሰ በላውን ቡድን ገጽታ ለመቀየር እንዲያስችል የገፅታ ግንባታ ላይ እንዲሰሩ በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ለመደለል በማለም መሆኑ ታውቋል። በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እየፈነዱ ባሉት ህዝባዊ አመፆችና ተቃውሞዎች ከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ የሚገኙት የህዋሓት ቱባ ሹማምንቶች በግል ግለሰቦቹን በመገናኘት የተለያዩ ድርጅታዊ ዲስኩሮችንና የድጋፍ ተማፅኖዎችን ሲያቀርቡ መሰንበታቸውንም ለማወቅ ችለናል። በዝግጅቱ ላይ ለታደሙት ከ150 በላይ ግለሰቦች የየቀን ወጪቸው ሙሉ በሙሉ ተሸፍኖላቸው፤ በተጨማሪም ከፍተኛ የቀን አበል እየተከፈላቸው ለዝግጅቱ ወደ ደደቢት ማምራታቸውም ተነግሯል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሰሞኑን በአገር ሐብት በደደቢት ቸበርቻቻ ሲሉ የሰነበቱትን አርቲስቶች በተመለከተ ኢትዮጵያውያን ብስጭታቸውን እየገለፁ ሲሆን የጥበብ ካባቸውን አውልቀው ለጨቋኝ፤ ዘረኛና ፀረ ኢትዮጵያ ድርጅት ካድሬ መስለው ውስኪ ሲራጩ፡ አሸሼ ገዳሜ ሲሉ መክረማቸው ለህዝብ ያላቸውን ከፍተኛ ንቀት ከማሳየቱም በላይ የግለሰቦቹን ሆድ አደርነት ያመለክታል ሲሉ በርካቶች ቁጣቸውን ሰንዝረዋል። በተለይ ግለሰቦቹ ለበአሉ

... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## በኦሮሚያ ልዩ ዞን በሰንዳፋ ከተማ በሺዎች የሚቆጠሩ ነዋሪዎች ለጎዳና ህይወት መዳረጋቸው ታወቀ

የፋሽስቱ ወያኔ ቤት አፍራሽ ግብረ ሐይል በኦሮሚያ ልዩ ዞን በሠንዳፋ ከተማ ከመቶ በላይ ህጋዊ ቤቶችን ያለምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ ማፈራረሱን ተከትሎ በሺዎች የሚቆጠሩ ነዋሪዎች ለዘመናት ከኖሩበት ቦታዎቻቸው በህገወጥ መንገድ ተፈናቅለው ለጎዳና ህይወት መዳረጋቸው ታውቋል። ነዋሪዎቹ በከተማው በህጋዊነት ቤት ቀልሰው ከ7 ዓመት እስከ 20 ዓመታት ድረስ መኖራቸው የታወቀ ሲሆን ሕጋዊ የግብር ደብተር እንዳላቸውና ለዘመናት ግብር ሲገብሩም መቆየታቸውን ለማወቅ ችለናል። ነዋሪዎቹ አቤቱታቸውን ለማሰማት ወደ ተለያዩ የአገዛዙ ተቋማት ቢሄዱም መፍትሔ ሊያገኙ አለመቻላቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በወረዳ ፓሊሶች አማካኝነት የግብር ደረሰኝ እና ደብተሮቻቸው ህጋዊ መሆኑን ለማረጋገጥ በኮምፒውተር እናመሳክር በሚል ማጭበርበሪያ ተወስዶባቸው እስካሁን እንዳልተመለሰላቸው ለማወቅ ተችሏል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በከተማው የተሾሙት የፋሺስቱ ወያኔ ቅጥረኞች ቦታዎቹን በልማት ስም ለመቀራመትና በሊዝ ለመቸብቸብ ዝግጅት ማጠናቀቃቸውን ምንጮቻችን አመልክተዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ህገ ወጡን የቤት ፈረሳ ተከትሎ በሰንዳፋ ከተማ ተቃውሞ መቀስቀሱ የታወቀ ሲሆን ጥቂት የማይባሉ አባወራዎች ህጋዊ ቤቶቻችንን አናስፈርስም በማለት ከልዩ ሐይል ፓሊሶች ጋር በፈጠሩት ቅራኔ ከፍተኛ ድብደባ እንደተፈጸመባቸው ለማወቅ ተችሏል። ለተቃውሞ የወጡ የአካባቢው ወጣቶችም በአገዛዙ ቅጥረኛ ፖሊሶች በጅምላ ታፍሰው ለእስር መዳረጋቸውን ያደረሱን ምንጮቻችን ወጣቶቹ በእስ ቤት ከፍተኛ ድብደባ እየተፈጸመባቸው እንደሚገኝም አመልክተዋል።

እብሪተኛው ወያኔ በመላ አገሪቱ በብዙ መቶ ሺዎች የሚገመቱ ዜጎችን ለዘመናት በህጋዊነት ከሚኖሩበት ቤቶታቸው በማፈናቀል ቤት አላባ በማድረግ ለከፋ ችግር እየዳረጋቸው እንደሚገኝ በተለያዩ ጊዜያት እየተከታተልን መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን ከዚህ ህገ ወጥ የመሬት ዘረፋ ጋር በተያያዘ ከላይ እስከ ታች የተሰገሰጉት የጉጅሌው ቱባ ሹማምንቶች ከፍተኛ ሐብት ማካበት መቻላቸው ይታወቃል።

## በምስራቅ ጎጃም ዞን የተቀሰቀሰው የተማሪዎች ተቃውሞ ተባብሶ በመቀጠሉ በዞኑ ከፍተኛ ውጥረት አይሏል

በምስራቅ ጎጃም ዞን በሁሉም ትምህርት ቤቶች የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች መደበኛ ትምህርታቸውን አቁመው እንዲወስዱ የተደረገውን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስልጠና ላይ ተቃውሞ ማሰማታቸውን ተከትሎ እብሪተኛው የወያኔ አገዛዝ የሐይል እርምጃ መውሰድ በመጀመሩ በዞኑ ከፍተኛ ውጥረት ነግሶ እንደሚገኝ ምንጮቻችን ከአካባቢው ያደረሱን መረጃ ያመለክታል። በተለይ በደብረ ማርቆስ፤ ባሶ ሊበን፤ ሞጣ እና በሌሎችም ከተሞች አገዛዙ ለተማሪዎች እስካሁን ሲሰጥ የቆየው የፖለቲካ ቅስቀሳ ምንም ውጤት አላስገኘም በማለት ተማሪዎቹ የስልጠና ቦታዎችን ጥለው የወጡ ሲሆን በአካባቢው የሰፈሩት ቅጥረኛ የፌደራል ፖሊሶች ተማሪዎቹ እየደበደቡ በጅምላ በማፈስ ወደ እስር እያጋዟቸው እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል። በድብደባው ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ተማሪዎች ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰባቸው የታወቀ ሲሆን በከተማዎቹ የተሰማሩት ቅጥረኛ ፌደራል ፖሊሶች አሁን ድረስ ህፃን፤ አዋቂ ሳይሉ በመንገድ ላይ የሚገኙትን ሰዎች ሁሉ እየደበደቡ በማፈስ ወደ እስር በማጋዝ መጠመዳቸውን ምንጮቻችን ተናግረዋል።

በመጭው ግንቦት በሚካሄደው ምርጫ ከወዲሁ ቤተሰቦቻቸው ድምጽ ለፋሺስታዊው አገዛዝ እንዲሰጡ እንዲያግባቡ የተጠየቁት ተማሪዎቹ በአንድነት ወያኔ ሌባ የሚል ጩኸት በማሰማት ለአገዛዙ ጥያቄ ያላቸውን ተቃውሞ በመሰንዘር የስብሰባ አዳራሾችን ጥለው መውጣታቸው ታውቋል። በተጨማሪም ተማሪዎቹ ለምን ጥላቻን የሚሰብኩና ለግጭት የሚጋብዙ ቅስቀሳ ትቀሰቅሳላችሁ፣ የወያኔ የተዛባ ፖሊሲ ምሁራንንም ጭምር ለስደት እየዳረገ ነው፣ ከቻይና እና ከኮሪያ የሚያስተሳስረን የታሪክም ሆነ የባህል መሰረት የለንም፤ የዘረኛው ሕወሓት አገዛዝ 24 አመት ሙሉ ያልተገበረውን ዴሞክራሲ ሊያስተምረን አይችልም በማለት በአገዛዙ ላይ ያላቸውን መራር ተቃውሞ አሰምተዋል።

## ቀኑ ሲቃረብ መውጫው ይጠባል!

ኢትዮጵያ ሀገራችን በታሪኳ ከአስከፊ የፈተና አረንቋ ውስጥ ተገፍታ የገባችበት ዘመን ቢኖር ይህ የምንገኝበት ዘመነ ወያኔ ብቻ ነው። ዜጎችዋ ከፋሽስት ኢጣልያ በከፋ ሁኔታ ይህ ቀረሽ የማይባል የመከራ መአት የወረደባቸውና እየወረ ደባ ቸው የሚገኙበት ዘመን ቢኖር ይህ የምንገኝበት ዘመን ወያኔ ብቻ ነው። እስር ቤቶች ሞልተው ተጨማሪ እስር ቤቶች መገ ንባት ከልማት ተቆጥሮ የሚፎከርበት ዘመን ቢኖር ይኸው ዘመነ ወያኔ ብቻ ነው። የሀገሪቱ ብሄራዊ ባንክ ንብረት የሆ ነው ወርቅ በባሌስትራ ለውጦ እስከ መዝረፍ የደረሰ በጠራራ ፀሀይ የህ ዝብና የሀገር ሀብት ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ በጥቂቶች የሚዘረፍበት ዘመን ቢኖር የምንገኝበት ዘመነ ወያኔ ብቻ ነው። የጅምላ እስር፤ የጅምላ ግድያ፤ የጅምላ ስደትና መፈናቀል፤ ይበልጡንም በታሪካችን ታይቶ በማያውቅ መልኩ ለሞት፤ ለእስር፤ ለመፈናቀልና ለስደ ት ምክንያቱ የተገኘንበት ዘውግ የሆነበት ዘረኛ ዘመን ቢኖር ይኸው ዘመነ ወያኔ ብቻ ነው።

ባጠቃላይ ላለፉት 23 አመታት ወያኔ ማድረግ የሚችለውን አስከፊ ነገር ሁሉ በሀገርና በህዝብ ላይ ሲፈፅም ቆይቷል። ዛሬ ከ23 አመ ታት በኋላ ሀገራችንና ህዝባችን ያልተዘፈቁበት የችግር ማጥ፤ ያልደረሰ የሀብትና የሰብአዊ ውድመት፤ ያልተፈፀመ የግፍና የሰቆቃ አይነት የለም። ወያኔ ይህን ሁሉ ሲፈፅም መሳሪያ አድርጎ ከተጠቀመባቸው ተቋማት ውስጥ ዋነኛዎቹ የመከላከያ፤ ፍርድ ቤትና የፖሊስና የደህንነት መሆናቸው ጥያቄ የለውም። የእነዚህ ተቋማት አባላት ከወያኔ ጥቃት ሰለባ ከመሆን ባይተርፉም የዚህን ወንጀለኛና ዘረኛ ቡድን እድሜ በአንድ ቀን በመጨመሩ ስራ ላይ ከፍተኛውን ድርሻ እንደያዙ ዛሬም መገኘታቸው አሌ የማይባል እውነት ነው። ይህ ሲባል ግን በሀገርና በህዝብ ላይ እየደረሰ ያለው ክህደት፤ ግፍና ሰቆቃ የሚያማቸው፤ መከራው መረራቸው፤ ብሶቱ ብሶታቸው የሆኑ አባላት የሉም ማለት እንዳልሆነ፤ ይልቁንም አብዛኛዎቹ የዚህ ስሌት ተካፋይ ስለመሆናቸው የሚጠራጠር የለም።

ነገር ግን ከህዝብ አብራክ በወጡና ልጆቹን ሳይመግብ በከፈለው ታክስ በተደራጀ የመከላከያ፤ የፖሊስና የደህንነት ተቋማት ውስጥ የምትገኙ አብዛኛውና የግፉ ቀማሽ የሆናችሁ አባላት ዛሬ የምትገኙበት ሁኔታ እንደ አለፉት 23 አመታት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፤ ከዛሬ ነገ የተሻለን ነገር ተስፋ በማድረግ፤ በግርግሩ ፍርፋሪ ሊወድቅልኝ ይችላል ከሚል ራስ ወዳድነት...... ወዘተ በመሳሰሉ በርካታ ምክንያቶች ለፍትህ፤ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ብሎም ለኢትዮጵያችን ቀጣይ ህልውና በሚደረጉ ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች ላይ በመቆም ብሎም የጥቂት ዘረ ኞች ስልጣንና ምቾት እድሜ ለማራዘም የተጓዛችሁበት መንገድ ብዙም ማስኬድ ከማያስችልበት፤ ይልቁንም ዛሬ ከሁለት መንታ መንገድ የ ደረሳችሁበትና ቆም ብሎም ማየትና ማገናዘብን ከሚጠይቅ ወቅት ላይ ትገኛላችሁ። አንዱ በዘረኝነት በትር እየተወቀጡ የወያኔ ሎሌ ሆኖ መቀጠል፤ ሌላው ከህዝብ አብራክ የተገኛችሁ ናችሁና ከህዝብ ወገን ተቀላቅሎ ሀገርን፤ ወገንንና ራስን ነፃ ለማውጣት መነሳት..

ለመከላከያ ሰራዊት፡- ላለፉት 23 አመታት ከጠመንጃ ተሸካሚነት ላለፈ ለማይፈልጉህ፤ ለአንተነትህ መለኪያው እውቀትህ፤ ችሎታ ህና አገልግሎትህ ሳይሆን የተገኘህበት ዘውግ መስፈሪያህ ለሆነበት ዘረኛ ስርአት፤ መቀየሪያ መለያ ልብስ ተነፍጎህ ቀዳዳ እየጣፍክ የልጆችህን የረሀብ ልቅሶ እያዳመጥክ በአንተ ትከሻ በዘረፉት ሀብት የገነቧቸውን ህንፃዎች ጠባቂ ላደረጉህ፤ ፍትህ ነፃነት ሲል በተራበ አንጀታቸውና በደ ከመ ድምፃቸው በጠየቁ ወገኖችህ ላይ ይህ ቀረ የማይባል ግፍ ሲያ ስፈፅምህ ለቆየው የወያኔ ዘረኛ ቡድን ዛሬም ተገቢውን ምላሽ የመስጠት እድሉ አለህ።አልረፈደምና ተጠቀምበት!!!

የፖሊስ ሰራዊት አባላት፤- ፍትህ ላሉ ጥይትን፤ ነፃነት ላሉ የጭካኔ በትርን፤ ሀገሬን ላሉ ከጨለማ ዘብጥያ መወርወርን.. ዋነኛ ተግባርህ በሆነበት በዚህ ዘረኛና በወንጀል የተጨማለቀ ስርአት ውስጥ የቆየህበት ያለፉት 23 አመታት ለአንተም፤ ለቤተሰብህም፤ ለተገኘህበት ህብረ ተሰብ ሆነ ለሀገርህ የፈየደው አንዳች ነገር ያለመኖሩን ይበልጡኑ ከእሳት ወደ እረመጥ ከሆነው የወያኔ ጉዞ ራስህን አውጥተህ ከህዝባዊው ወገን የምትቀላቀልበት የመጨረሻው ሰአት መሆኑን ተገንዝበህ ምርጫህን ከወገንህ አድርግ። ለአንተም አልረፈደም!!

የደህንነት አባላት፡- ለሀገር ደህንነት ለህዝብ ሰላም ሲባል በህዝብ ሀብት በተደራጀ ተቋም ተጠቅመህ በሀገርህ ላይ ክህደትን፤ በወገ ንህ ላይ ግፍና ሰቆቃን ስትፈፅም መቆየትህ ከወንጀሎች ሁሉ የከፋ ወንጀል መሆኑን ተገንዝበህ ለፍትህ ለነ ፃነትና ለዲሞክራሲ ሲሉ በተነሱ ወገኖችህ ላይ ስትሰነዝር የቆየኸውን በትር በፍትህ በነፃነትና በዲሞክራሲ ላይ በቆሙት ዘ ረኛ አዛዦችህ ላይ የማሻው ጊዜ አሁን ነው። ስለ ዚህም ከህዝባዊው ወገን ተቀላቅለህ ህዝባዊ ወገንተኝነትህን የምታሳይበት ብሎም የበደልከውን የምትክስበት ጊዜውም እድሉ አለህና ተጠ ቀምበት።ላንተም አልረፈደም!!

በመጨረሻም ልጇን የምትጠላ እናት፤ ወገኑን የሚገፋ ህዝብ፤ ዜጎቹን የማይቀበል ሀገር የለምና ይህን በአስከፊነቱ ወደር የማይገኝለት የወያኔ ዘረኛ ስርአት ደግፎ ማቆየት ከማይቻልበት ይበልጡንም እንደ ትሪፖሊና ኢያሪኮ የግፈኞች ግንብ በህዝባዊ ሀይል ከሚገረሰሰበት ከመጨረሻዋ ደቂቃ ከመደረሱ በፊት ከእናታችሁ እቅፍ ከወገናችሁ መሀል ግቡ!! ተቀላቀሉ!! ቀኑ ሲቃረብ መውጫው ይጠባልና ጊዜ ሳታጠ ፉ ፈር ቀዳጅ ወንድሞቻችሁን መከተል ብልህነት ነው እንላለን!!!

የኢያሪኮም የጋዳፊም ግንብ ተንዷል፤ የወያኔም ይናዳል!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## ወያኔ በየከተማዉ ከፍተኛ ተቃውሞን እያስተናገደ መሆኑ ተሰማ

በደቡብ ጎንደር በሚገኙ መሰናዶች የሚማሩ ተማሪዎች በበኩላቸው አስገዳጅ ስልጠና በመደበኛው የትምህርት ሰአታቸው እንዲሰጥ መደረጉን እየተቃወሙ ሲሆን በተጨማሪም አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ስለምን ራሱን ከደርግ ጋር ብቻ ያወዳድራል? ልማታዊ መንግስት የሚባለው ብሄርን ከብሄር ጋር የሚያጋጭ ነው ወይስ አንድ ኢትዮጵያን የሚፈጥር? አገዛዙ የመምህራንን መብት ማክበር የሚጀምረው መቼ ነው? ከውጭ አገር በአማርኛ የሚተላለፉ የኢትዮጵያ ሚዲያዎች ለምን ይታፈናሉ? የሚሉ ጥያቄዎች በማንሳት ቅጥረኛ የአገዛዙ ጅሌዎችን አንገት ማስደፋታቸው ታውቋል። ስብሰባዎቹም ያለ ምንም ስምምነት መበተናቸውን ከስፍራው የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

በደቡብ ወሎ በሚገኙ አንዳንድ የመሰናዶ ትምህርት ቤቶችም በተመሳሳይ መልኩ አስገዳጅ ስልጠናው ባለመግባባት የተበተነ ሲሆን ውጥረት ውስጥ የሚገኙው የጉጅሌው ወያኔ ቅጥረኞች በተማሪዎች ላይ ከፍተኛ ማስፈራራትና ዛቻ እያደረሱባቸው እንደሚገኙ ለማወቅ ችለናል። በኮምቦልቻ ተማሪዎች የአገዛዙን ቅጥረኛ ካድሬዎች በጥያቄ ከማፋጠጥ ጀምሮ በአገሪቱ ውስጥ በሚታየው ዘረኝነት፣ የፍትህ እጦትና ሙስና ላይ አስተያየቶችን የሰጡ ሲሆን ተማሪዎቹ ከስብሰባው መጠናቀቅ በሁዋላ ህዝቡን ለአመጽ ለማነሳሳት አስባችሁዋል በሚል ማስጠንቀቂያና ባስፈራሪያ ዛቻ እንደደረሳቸው ዘጋቢያችን ታውቋል። የብሄር ግጭትን በተመለከተ ዋናው ተጠያቂው ወያኔ ነው ያሉት ተማሪዎች፣ በተለይ የትግራይን ህዝብ ከአማራውና ከኦሮሞው ጋር ለማጋጨት በአገዛዙ የሚጎለጎለው ሴራ በሁዋላ ላይ አገሪቱን ይጎዳታል ሲሉ አስጠንቅቀዋል። የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ አያያዝ በአገራችን ፍትህ እንደሌለ የሚያሳይ ነው በማለት የፍትህ ስርአቱን የተቹት የኮምቦልቻ መሰናዶ ተማሪዎች፣ አቶ አንዳርጋቸው ከስድስት ወራት የእስር ጊዜ በሁዋላ፣ በቤተሰብና በጠበቃ እንዳይጎበኙ፣ የታሰሩበትም እንዳይታወቅ መደረጉ የፍትህ ስርአቱ በአገራችን መቀበሩን ያሳያል ሲሉ ምሬታቸውን አሰምተዋል።

በጎንደር ከተማ የሚገኙ ተማሪዎች በበኩላቸው ቅጥረኛ የወያኔ ጀሌዎች በስብሰባው ላይ መገኘት አለባችሁ ብለው ቢያስፈራሩዋቸውም "አንገኝም" በሚል በአንድ ድምጽ ተቃውሞ አሰምተው በተመሳሳይ መልኩ ስብሰባው ረግጠው መውጣታቸውን ዘጋቢያችን ያደረሰን መረጃ አመልክቷል። በእስቴ ወረዳ የሚገኙ መምህራንም ለአስገዳጁ ስልጠና ቢጋበዙም አሻፈረኝ በማለት ስብሰባውን ረግጠው መውጣታቸው ታውቋል።

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በአማራ ክልል በተለያዩ ከተሞች እያስተናገደ የሚገኘው መራር የተማሪዎች ተቃውሞ ከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ ከቶት እንደሚገኝ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በተለይ በአንዳንድ የክልሉ ከተሞች እየተሰተዋሉ ያሉት የእንቢተኝነት እንቅስቃሴዎች ከዕለት ዕለት እየተባባሱና እየተቀጣጠሉ በመሄዳቸው በክልሉ ህዝባዊ ህዝባዊ አመጽ ሊከሰት ይችላል በሚል ስጋት ቱባ ጉጅሌዎች እንቅልፍ አጥተው ቅጥረኛ የፌደራል ፖሊሶችን በየ ከተሞቹ የማሰራጨት ስራ በመስራት ላይ እንደሚገኙ የውስጥ ምንጮችን አመልክቷል።

## ብሶት የወለደን፣ ብሶት የምንወልድ

በኤፍሬም እሸቴ

> *"የድሀውን ጩኸት እንዳይሰማ ጆሮውን የሚደፍን ሰው፥ እርሱ ራሱ ይጮኻል አይሰማለትምም።" (መጽሐፈ ምሳሌ21፥13)*

እኛ እንዲህ ያለን ሕዝቦች ነን። "ብሶት የወለደው" የሚያስተዳድረን፣ ብሶት አርግዘን ብሶት የምንወልድ፣ በብሶት አገር የምንኖር ሕዝቦች። ብሶት የወለደን፤ አባት እናታችን ብሶቶች የሆኑ ሕዝቦች። ሰው ወላጁን መቀየር እንደማይቻለው፣ የብሶት ልጅ ብሶት እንጂ የብሶት ልጅ ደስታና ርካታ እንደማይሆነው ሁሉ እኛ ብሶቶችም ብሶትን አምጠን ብሶት እንወልዳለን። ብሶቶቻችን ከምሬትና መከፋት ጋር ይጋቡና እልቂት እና ውድመትን ያፈራሉ። ከብሶት አዙሪት ያልወጣ አገርና ሕዝብ ፍጻሜው ሳይታለም የተፈታ ነው።

ግንቦት1983 ዓ፣ም ሐዋሳ ከተማ በእግሬ እየተጓዝኩ፣ ከአንድ ሱቅ በትልቁ በተለቀቀ ሬዲዮ የሰማኹት የዚያ ተጋዳላይ ድምጽ እና ያቺ ብሶት የምትለው ቃል አሁን ድረስ በጎሊናዬ አለች። በረኸኞቹ ሬዲዮ ጣቢያውን ሲቆጣጠሩ ያንን መልእክት ለማሰማት ቀድመው የተዘጋጁበት ይሁን አይሁን ባላውቅም፣ በቃላት ምርጫ ደረጃ "ብሶት"ን መጠቀማቸው በብዙው ገላጭ ነበር። ነፍጥ አንግበው ትግል የገጠሙት ብሶት ፈንቅሏቸው እንደሆነ ለማጠየቅ፣ ሌላ ምንም አማራጭ እንዳልነበራቸው ለማስረገጥ የሚችል ጥሩ ቃል ነው።

ብሶት፡- ባሰ ከሚል ግስ የሚመዘዝ መቀየምን፣ መበሳጨትን፣ ማዘንን፣ መከፋትን የሚያመለክት ነገር ነው። ተራ መከፋት ብቻ ሳይሆን ከፍ ያለ ቅሬታ ነው። ሰዎች የሚፈልጉትን ባለማግኘታቸው የሚፈጠር ቅሬታ። የሚፈልጉትን ባለማግኘታቸው ብቻ ሳይሆን የሚገባቸውን፣ የራሳቸው የሆነውን ባለማግኘታቸው፣ ከዚያም አልፎ ሊደርስባቸው የማይገባ ነገር ሲደርስባቸው የሚፈጠር ጠንካራ ስሜት ነው።

እንዲህ ያለው ከፍ ያለ ብሶት በቀላሉ የሚፈጠር ተርታ ቅሬታ አይደለም። በተግባር የደረሰም ይሁን በታሪክ እየተነገረ አሁን እንደተፈጠረ ተደርጎም ቢቆጠር "ብሶት" ሆድ አንጀትን አላውሶ ሞትን የሚያስመርጥ፣ ብረት የሚያስነሣ፣ ከአገር የሚያስሸፍት፣ ከዘመድ ባዳ ከአገር ምድረ በዳ የሚያሰኝ "ሮሮ" ነው። ያውም የጽኑዕ በደል ውጤት። መጽሐፉ እንዳለው "ከፀሐይ በታችም የሚደረገውን ግፍ ሁሉ አየሁ እነሆም፥ የተገፉት ሰዎች እንባ ነበረ የሚያጽናናቸውም አልነበረም በሚገፉአቸውም እጅ ኃይል ነበረ፥ እነርሱን ግን የሚያጽናናቸው አልነበረም።" (መጽሐፈ መክብብ4፥1)

ብሶት ላይ አምጸው የተነሡ ሰዎች ራሳቸውም በእነርሱ ላይ ይፈጸም የነበረውን በደል ለመድገም የሚችሉበት ዕድል እጅግ ከፍ ያለ መሆኑን የአገራችን ታሪክ ጥሩ እማኝ ነው። በበደል ውስጥ ያለፉ ሰዎች የሚቃወሙት በጠቅላላው በደልን ሁሉ ነው ወይንስ እነርሱ ላይ የሚደርሰውን በደል ነው? "እኔን ምንም አይንካኝ ሌላው እንደፈቀደው" ነው ወይንስ "በእኔ ላይ እንዲደርስ የማልፈልገውን በማንም ላይ እንዲደርስ አልፈልግም" ከሚል ሐሳብ?

የራሳቸው ወገን ሲነካ ተቆጭተው የተነሡ ሰዎች፣ ያው በደል በሌላው ወገን ላይ ሲደርስ የማይቆረቁራቸው ከሆነ፤ በራሳቸው እምነት ላይ የተፈጠረው አደጋ በሌላው እምነት ላይ ሲጋረጥ የማይከነክናቸው ሰዎች በትክክል በደል እና ብሶት ገብቷቸዋል ማለት ይቻላል?

ትናንት የበደሉን ሰዎች በብረታቸው ይመኩ እንደነበረ እናውቃለን። እንኳን ጥቃቅን የአገር ውስጥ ተቃዋሚዎች ከአፍሪካ ከየትኛውም ጥግ ጦር ቢነሣ ወገቡን ሰብረን እናስቀረዋለን እንደተባለ እናውቃለን። እነዚያው የተናቁት የአገር ውስጦቹ ወንበሩን እንደገለበጡም እናውቃለን።

ታዲያ እነዚያው የተናቁት በፈንታቸው ሌላውን "ከፍ ብለን አንገትህን ዝቅ ብለን ባትህን እንቆርጣለን፤ ገና ምኑን ዓይተህ ለልጅ ልጅ እንገዛሃለን፣ አርቀን ስለቀበርንህ በየት ልትወጣ" ሲሉ መስማት ጥላቸው ከበደልና ከግፍ ጋር ሳይሆን ከአንድ በዳይ ጋር ብቻ መሆኑን አያስረግጥም?"እኔን እንዳትነካኝ፣ እኔ ግን ሌላውን እንደፈለግሁ ላድርገው" የሚል የደካማ ፍልስፍና? ጥያቄው "በደል አይኑር" ሳይሆን "በዳዩ እኔ ልሁን"፤ "ረሃብ አይኑር" ሳይሆን "እኔ ብቻ ልጥገብ"፣ "ድህነት አይኑር" ሳይሆን "እኔ ብቻ ሀብታም ልሁን"፣ "ብሶት አይኑር"ሳይሆን "ብሶተኛው እኔ አልሁን" የሚል ግላዊና ቡድናዊ ጉዳይ ይሆናል።

በደል ለመፈጸም አቅምም ፈቃድም ያላቸው ሰዎች ራሳቸውን ለኅሊናቸው አስገዝተው "የሠራኹት ስሕተት ነው" ለማለት እጅግ ከባድ የኅሊና ልዕልናን ይጠይቃቸዋል። የጠገበ ሰው የተራበ ሊኖር ይችላል ብሎ እንዲያስብ፣ የብሶተኛውን ዕንባ ሲያይ በርግጥም ተበድሎ ሊሆን ይችላል እንዲል፣ ከሚያውቃቸው በዳዮች ይልቅ ለማያውቃቸው ብሶተኞች ጥብቅና እንዲቆም ከፍ ያለ ዕውቀት ይፈልጋል። በርግጥም የወደፊቱን በጥንቃቄ ለመገመት መሞከርንና ውጤቱን ከወዲሁ ለማመዛዘን መፍቀድን ይጠይቃል።

ብሶት መፍትሔ የሚያገኘው ለትክክለኛው ብሶት ትክክለኛውን መፍትሔ በማስቀመጥ ብቻ ነው። ጊዜያዊ ማዳፈን እና ማድበስበስ በጭራሽ መፍትሔ አይሆንም። የሚያለቅሱ ሰዎችን ለምን አለቀሳችሁ፣ ለምን አነባችሁ በሚል ማስፈራሪያ ዕንባቸውን ወደ ውስጣቸው እንዲውጡ ማድረግ ይቻል ካልሆነ በስተቀር ሳጋቸውንና ብሶታቸውን ማጥፋት አይቻልም። የሁል ጊዜውም ተረት "ውሻህን ለመቅጣት በር አትዝጋ" ነው። መውጫ ቀዳዳ ተውለት። መውጫ፣ መተንፈሻ ሲያጣ ወደራስህ እንዳይመለስ። አገር ለማስተዳደር፣ ሰዎችን ለመምራት፣ ውሻን ከመግራት ያነሰ አካሄድ መሔድ ውጤቱን አስከፊ ያደርገዋል። የጊዜ ጉዳይ ብቻ ካልሆነ በስተቀር የታወቀ የተረዳ ነገር ነው።

እንኳን በአገር ደረጃ በግለሰብ እና በቤተሰብ ደረጃ እንኳን ብሶት ማዳመጥ እና ትክክለኛ መፍትሔ መስጠት አዋቂነት እንጂ ተሸናፊነት አይደለም። ባል ወይም ሚስት ችግር አለብኝ፣ ደስተኛ አይደለሁም እያሉ አንድኛው ወገን ለመስማት ፈቃደኛ ካልሆነ ያ ትዳር ሰላም እንደማይኖረው ግልጽ ነው። አንድ መሥሪያ ቤት የሠራተኞቹን ብሶት ሰምቶ ትክክለኛ መፍትሔ ካልሰጠ ቢያንስ ውጤታማነቱ ላይ ጉዳት እንደሚያስከትልበት ይታወቃል። አገርም እንደዚያው ነው። የዜጎችን ብሶት የማይሰማ መንግሥት ምን እስከ አፍንጫው ቢታጠቅ መንበርከኩ አይቀርም። ሮሮን በኃይል ማዳፈን አይቻልም።

የሰው ብሶት በአንደበቱ ባይነገር ፊቱ፣ ኑሮው፣ ሕይወቱ ይናገራል። በዝምታ ይጮኻል። በዝምታ ያለቅሳል። በዝምታ አቤ.....ት ይላል። የጥንት ገገሮች "እረኛ ምን አለ? አዝማሪ ምን አለ?" የሚሉት የሕዝቡን የዝምታ ጩኸት ለማዳመጥ ነው። ትዕግስተኛው ኢዮብ "የዝምታ ድምጽ ሰማሁ" ያለው አለነገር አልነበረም (መጽሐፈ ኢዮብ 4፥16) ። ለካስ ዝምታም ድምጽ አለው!!! ጋቢውን አፉ ላይ ጣል አድርጎ የሚሰማህ ባለዝምታ ሰው በርግጥ እየጮኸብህ መሆን አለመሆኑን ጠይቅ። የሰማህ ሁሉ አያዳምጥህም። ያጨበጨበልህ ሁሉ አይደግፍህም። የታዘዘልህ ሁሉ አይስማማልህም። ቀን ነው የሚጠብቅልህ።

ስለዚህ የዝምታ ጩኸቶችን ስማ። ያለ ዕንባ የሚያለቅሱ ዓይኖችን ተመልከት። ባይቃወሙህም የማይደግፉህን ሰዎች ሐሳብ አዳምጥ። ለምን ተዘረፍኩ ብለህ ዛሬ መዝረፍህ፣ ለምን ተገፋሁ ብለህ ዛሬ ገፊ መሆንህ፣ ለምን ተገደልኩ ብለህ ዛሬ ገዳይ መሆንህ፣ ለምን ተራብኩ ብለህ ዛሬ አለመጥገብህ ከታሪክ አለመማርህን እንጂ ጉብዝናህን አያመለክትም። ብሶቶችን አብርድ፣ ግፍ በደሉን ተው። አንተን የወለደ ብሶት ሌሎችን መውለዱን ግን በፍጹም አትጠራጠር።

……………………………………………………………………………

## በጉጅሌው ወያኔ ቱባ ሹማምንት መካከል አለመተማመን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄዱ ታወቀ

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ከመላው አገሪቱ ለተውጣጡ የድርጅቱ ከፍተኛ ሹማምንት መጪውን የይስሙላ ምርጫ በተመለከተ በናዝሬት ከተማ ስልጠና በመስጠት ላይ ሲሆን፣ ከስልጠናው በፊት ማንኛውም የአገዛዙ ሹማምንት ስልክ ይዞ መግባት እንደማይችል ጥብቅ የሆነ መልእክት መተላለፉን ተከትሎ ሁሉም የአገዛዙ ሹማምንቶች ስልካቸውን እና ማንኛውንም አይነት የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ጥለው ለመግባት መገደዳቸውን የውስጥ ምንጫችን ያደረሰን መረጃ ያሳያል። ወደ ስብሰባው በሚገባ ማንኛውም ቅጥረኛ ሹማምንት ላይ ጥብቅ ፍተሻ እየተደረገ እንደሚገኝ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ይህም ጥቂት የማይባሉ የክልልና ከተማ አስተዳደር ሹማምንትን ከዞን ጀምሮ ያሉ የስራ አመራሮችንና የድርጅቱ ዋና ዋና የሚባሉ ቅጥረኛ ካድሬዎች ማስኮረፉን ምንጫችን አመልክቷል። ይህ ትእዛዝ የተላለፈውም የጉጅሌው ወያኔ ታላላቅ ስብሰባዎች ሳይቀር እየተቀረጹ ለተቃዋሚ የነፃነት ሐይሎችን ጨምሮ ለተለያዩ በመገናኛ ብዙሃን መቅረባቸው ቱባ ጉጅሌዎችን እያበሳጨ በመምጣቱ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። በጉጅሌዎች መካከል አለመተማመኑ ስር ሰዶ እዚህ ደረጃ ላይ መድረሱ የአገዛዙን የመጨረሻ መውደቂያ ጊዜው ላይ መሆኑን ያሳያል ሲል ዘጋቢያችን ትዝብቱን ጨምሮ አድርሶናል።

## ወያኔ ጋምቤላ ዉስጥ 79 ሰዎች መግደሉን አመነ

የወያኔ አገዛዝ በጋምቤላ ክልል በጎደሬ ወረዳ ከመጋቢት እስከ ጳጉሜ በነበሩት ግጭቶች የተገደሉት ሰዎች ቁጥር ከ12 አይበልጥም በማለት በተደጋጋሚ ሲገልጽ ቢቆይም፣ አቃቢ ህግ የክልሉን ባለስልጣናት ለመክሰስ ባቀረበው የክስ ቻርጅ ላይ 79 ሰዎች መገደላቸውን ፣ 273 ቤቶች መቃጠላቸውን ከ13 ሺ በላይ ዜጎች እንዲፈናቀሉ ማድረጋቸውን ገልጿል። አንዳንድ ወገኖች የተገደሉት ሰዎች ቁጥር በመቶዎች እንደሚቆጠሩ ሲገልጹ፣ ኢሳት 60 ሰዎች መገደላቸውንና የሟቾቹን ስም ዝርዝር ይፋ በማድረግ ዘገባ አቅርቦ ነበር።

አቃቢ ህግ መንግስት አምኖ የሾማቸው የክልሉ ባለስልጣናት ግድያውን እንዳስፈጸሙና ግጭት እንዲነሳ እንዳደረጉ በክስ ቻርጁ ላይ አምልክቷል። የክልሉ ልዩ ሃይል አዛዥ አቶ ያእቆብ ሸራተንና የመዠንገር ዋና አስተዳዳሪ አቶ ትንሳኤ ራጃን ጨምሮ 35 የክልሉ ባለስልጣናት ክስ ተመስርቶባቸዋል። የክልሉ ባለስልጣኖች በሚጤ ህዝቡን ሰብስበው ከተለያዩ የሃገሪቱ ክልሎች የመጡ ሰዎች የእርሻ ቦታቸውንና የቡና ተክላቸውን ለክልሉ ተወላጆች እንዲያካፍሉ፣ ይህን የማያደርጉ ከሆነ ግን ከክልሉ እንዲወጡ ቅስቀሳ ማድረጋቸው በክሱ ላይ ተመልክቷል።

የግጭቱ መነሻ በአካባቢው የሚታየው መሬት ወረራ መሆኑ በተደጋጋሚ ቢገለጽም፣ በዚህ በኩል ተጠያቂ የሆኑ የፌደራል መንግስት ባለስልጣናት ለፍርድ አለመቅረባቸው የፍርድ ሂደቱ ተአማኒነት እንዲያጣ አድርጎታል። የቀድሞ የህወሃት አዛዦች የአካባቢው መሬት በስፋት እየቀሙና ነዋሪውን እያፈናቀሉ መሆናቸው በተጨባጭ ማስረጃ ቢረጋገጥም እስካሁን ምንም አይነት እርምጃ ሳይሰወድባቸው መቅረቱ በዜጎች መካከል ያለውን ልዩነት የሚያሳይ መሆኑን አዲስ አበባው ዘጋቢያችን አስተያየቱን አስፍሯል።

## በአዳማ በሚካሄደው ስብሰባ የኢህአዴግ ከፍተኛ ባለስልጣናት ሳይቀሩ ሞባይል ስልክ ይዘው እንዳይገቡ ተከለከሉ

ኢህአዴግ ከመላው አገሪቱ ለተውጣጡ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮች መጪውን ምርጫ በተመለከተ ስልጠና እየሰጠ ሲሆን፣ ከስልጠናው በፊት ማንኛውም ባለስልጣን ስልክ ይዞ መግባት እንደማይችል ጥብቅ የሆነ መልእክት በመተላለፉ፣ ሁሉም ባለስልጣናት ስልካቸውን መኪናቸው ውስጥ እየተዉ ወይም ለሹፌሮቻቸው እየሰጡ መግባታቸው ታውቋል።

ወደ ስብሰባው የሚገባ ሰው ማንኛውንም አይነት የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን መያዙንና አለመያዙን ለማረጋገጥ ጥብቅ ፍተሻ እንደሚካሄድበት የክልሉ ዘጋቢያችን ገልጿል። በገልማ አባ ገዳ አዳራሽ በሚካሄደው ስብሰባ ሚኒስትሮች፣ የሁሉም የክልልና ከተማ አስተዳደር መስተዳድሮችና ከዞን ጀምሮ ያሉ የስራ አመራሮችና የድርጅቱ ዋና ዋና ካድሬዎች ተገኝተዋል። ተሰብሳቢዎቹ ምንም አይነት ሞባይል ስልክ ወደ አዳራሽ ይዘው እንዳይገቡ መከልከላቸው ከዋናው አጀንዳው ይልቅ መነጋገሪያ መሆኑን የሚገልጹት ምንጮች፣ ትእዛዙ የተላለፈውም የኢህአዴግ ስብሰባዎች እየተቀረጹ በመገናኛ ብዙሃን መቅረባቸው የድርጅቱን አመራሮች እያበሳጨ በመምጣቱ ነው።

## የኢንተርኔት እና የተንቀሳቃሽ ስልክ መረጃዎች ላይ ጠበቅ ያለ ቁጥጥር የሚያደርግ አዋጅ ተረቀቀ

በሥራ ላይ ያለውን የብሮድካስት አዋጅ የሚሽርና ለመጀመሪያ ጊዜ በኢንተርኔት ድረገጾች እንዲሁም ተንቀሳቃሽ ስልክንበመጠቀም የሚቀርብ የብሮድካስት አገልግሎቶችን ላይ ጥብቅ ቁጥጥር የሚያደርግ የሚዲያ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቷል። የኢትዮጵያ የብሮድካስት ባለስልጣን ያዘጋጀውና በዚህ ዓመት ለፓርላማው ቀርቦ ይጸድቃል ተብሎ የሚጠበቀው ይህው የሚዲያ ረቂቅ አዋጅ አሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙሃን ማለትም ራዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ የኢንተርኔት ድረገጾች እንዲሁም የሕትመት ሚዲያውን የሚመለከት ነው። በዚህ አዋጅ ለመጀመሪያ ጊዜ የአንተርኔት ድረገጾች ፈቃድ ማውጣት የግድ መሆኑን ደንግጎአል።

በኢንተርኔት፣ በተንቀሳቃሽ ስልክ ወይም በመሰል የመረጃ መረብ አማካኝነት ለስርጭት የሚቀርብ ማንኛውም ፕሮግራም በአገር አንድነትና ሉአላዊነት ላይ አደጋ የሚጥል፣ በአገር ደህንነት፣ ክብርና ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያደርስ፣ የአገር ሚስጢርን የሚገልጽ፣ አመጽና ጦርነትን የሚቀሰቅስ፣ የሰው ልጆችን ስብዕና፣ ነጻነት ወይንም ስነምግባር የሚጻረር፣ የሌሎችን እምነት የሚያንኳስስ መሆን እንደሌለበት ደንግጎአል።

በተጨማሪም ሥራዎቹ ማንኛውንም የህብረሰተብ ክፍል፣ ብሔር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ጾታ፣ ዘር፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ማህበራዊ አመጣጥ፣ ወይንም ሌላ መሰል አቋምንና ክብርን የሚነካ ወይም የሚያዋርድ፣ በህዝቦችና በሃይማኖቶች መካከል የእርስ በእርስ ግጭት የሚቀሰቅስ ወይንም ጥላቻ የሚያስፋፋ፣ የግለሰብን ስም የሚያጠፋ፣ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን አመለካከት ስሜት የሚጎዳና ወደአልተፈለገ አቅጣጫ እንዲያዘነብሉ የሚገፋፋ፣ የህብረሰተቡን ሞራል የሚጥስ ወይንም በሕግ የተከለከለ ማንኛውንም ድርጊት የሚፈጽም መሆን የለበትም ይላል።

ተጠያቂነትም በተመለከተ ረቂቅ አዋጁ እንዳሰፈረው በኢንተርኔት፣ በተንቀሳቃሽ ስልክ ወይም በመሰል መረጃ መረብ አማካይነት የቀረበ ፕሮግራም ለሚያስከትለው ማንኛውም የወንጀል ድርጊት ወይም የፍትሐብሄር ጉዳት የፕሮግራሙ ሃላፊና የብሮድካስት አገልግሎት ሰጪው በአንድነት ተጠያቂ ይሆናሉ ይላል። በኢንተርኔት፣ በተንቀሳቃሽ ስልክ ወይም በመሰል መረጃ መረብ አማካይነት የቀረበ ፕሮግራምን ቁጥጥርን በተመለከተ ከህብረተሰቡ በቅሬታ መልክ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን የመመርመር፣ተቆጣጣሪ የመመደብ ስልጣን ወደፊት ለሚቋቋመው ባለስልጣን መ/ቤት ሃላፊነቱን ይሰጣል።

ረቂቅ አዋጁ የቴሌቪዥንን ከአናሎግ ወደዲጂታል ሽግግርን ለማቀላጠፍና የግል ቴሌቪዥን ለመፍቀድ ይረዳል ተብሎአል። በዚህ ረቂቅ አዋጅ መሰረት ተጠሪነቱ ለጠ/ሚኒስትሩ የሆነ የኢትዮጵያ የሚዲያ ባለስልጣን የሚባል መ/ቤት ይቋቋማል።የብሮድካስት አግልግሎት የሚመራበትን ሥርዓት ለመደንገግ ከ15 ዓመታት በፊት የወጣው አዋጅ ቁጥር 178/1991 የግል ቴሌቬዥን ጣቢያ ፈቃድ ለግል ባለሃብቶች የፈቀደ ቢሆንም ይህ ተግባራዊ ሳይሆን አዋጁ በቁጥር 533/1999 የተሻሻለ መሆኑ ይታወቃል። በተሸሻለውም አዋጅ ቢሆን የግል ቴሌቭዥን ጣቢያ የተፈቀደ ቢሆንም ኢህአዴግ መራሹ መንግስት ኢትዮጵያ ለዚህ ደረጃ ገና አልበቃችም በማለት አዋጁ እንዳይፈጸም እስካሁን ድረስ መከልከሉ የሚታወቅ ነው።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz
ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።
ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## የግብፅ ፕሬሲዳንነት የህዳሴዉ ግድብ ግብፅን እንደማይጎዳ ኢትዮጵያ በሰነድ እንድታረጋግጥ ጠየቁ

በያዝነዉ የፈረንጆቹ አዲስ አመት መጀመሪያ ላይ ኢትዮጵያን ይጎበኛሉ ተብለዉ የሚጠበቁት የግብፁ ፕሬዚዳንት አብዱልፈታህ አልሲሲ ኢትዮጵያ አባይ ወንዝ ላይ የምትገነባዉ ግድብ የግብፅ የውኃ ድርሻ እንደማይጐዳ በሰነድ እንድታረጋግጥ እንፈልጋለን ብለዋል ሲል አገር ዉስጥ የሚታተመዉና አፍቃሪ ወያኔ የሆነዉ ሪፖርተር ጋዜጣ ዘገበ። ፕሬዚዳንቱ ባለፈው ሰኞ ከሦስት የግብፅ መንግሥት ጋዜጦች ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ፣ በኢትዮጵያና በግብፅ መካከል በአሁኑ ወቅት መልካም ግንኙነት መኖሩን አስረድተዋል። እ.ኤ.አ. በጃንዋሪ 2015 ፕሬዚዳንቱ ይፋዊ የሥራ ጉብኝት ከሚያደርጉባቸው አገሮች መካከል ኢትዮጵያ አንዷ መሆኗን ገልጸዋል። ከኢትዮጵያ በተጨማሪ ፕሬዚዳንቱ ኩዌትን፣ ባህሬንና የተባበሩት ዓረብ ኤምሬትስን እንደሚጐበኙ አስታውቀዋል። ፕሬዚዳንቱ ኢትዮጵያን በሚጐበኙበት ወቅትም በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዙሪያ ውይይት እንደሚደረግ በሰጡት ቃለ ምልልስ ገልጸዋል። “እኛ የምንጠይቀውና የምንፈልገው ኢትዮጵያ ግድቡ የግብፅን የውኃ ድርሻ እንደማይጐዳ በቃል የሰጠችውን ዋስትና በሰነድ እንድታረጋግጥ ነው፤” ብለዋል።

የኢትዮጵያ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድን ከሳምንት በፊት ግብፅን ሲጎበኝ፣ ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ መጠቀምንና የህዳሴው ግድብ በግብፅ ላይ ጉዳት እንደማያደርስ መግለጹ ይታወሳል። ፕሬዚዳንቱም አገራቸው ግብፅ የኢትዮጵያን ከድህነት መላቀቅና መልማት እንደምትፈልግ ገልጸው፣ ግብፅ በውኃ እጥረት እንዳትጎዳ ጥንቃቄ እንዲደረግ ጠይቀዋል። በተጨማሪም የኢትዮጵያን ግድብ መገንባት እንደማይቃወሙም መናገራቸው አይዘነጋም። የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ድኑ መሪ አፈ ጉባዔ አባዱላ ገመዳ የግብፅ ፕሬዚዳንት ኢትዮጵያን እንዲጐበኙና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ንግግር እንዲያደርጉ በድጋሚ ጋብዘዋቸዋል። ፕሬዚዳንት አልሲሲ ኢትዮጵያን እንዲጐበኙ ጥሪ የቀረበላቸው በጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ አማካይነት ባለፈው መስከረም ወር መሆኑ ይታወሳል።

ፕሬዚዳንቱ በቃለ ምልልሳቸው፣ ‹‹ኢትዮጵያ የግብፅን የውኃ ድርሻ እንደማትጐዳ በቃል የሰጠችውን ዋስትና በሰነድ እንድታረጋግጥ እንፈልጋለን፤›› ቢሉም፣ ኢትዮጵያ ግን የግብፅ የውኃ ድርሻን በተመለከተ የሰጠችው የሰነድ ዋስትና አለመኖሩን ባለሙያዎች ይናገራሉ። የዓባይ ተፋሰስ አገሮች በኡጋንዳ የተፈራረሙትና ኢትዮጵያና ሩዋንዳ በፓርላማቸው ያፀደቁት የዓባይ ተፋሰስ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት (CFA)፣ የተፋሰሱ አገሮች ውኃውን በሚጠቀሙበት ጊዜ በሌላው የተፋሰስ አገር ላይ ጉልህ ጉዳት ማድረስ የሌለባቸው መሆኑንና ኢትዮጵያ የምትከተለውም ይህንኑ መሆኑን ባለሙያዎቹ ጠቁመዋል። የግብፅ ፕሬዚዳንት በሰጡት ቃለ ምልልስ ላይ የሩሲያው ፕሬዚዳንትና የጃፓኑ ጠቅላይ ሚኒስትር በዚሁ በጃንዋሪ ወር ግብፅን የሚጐበኙ መሆኑን ጠቁመዋል። ፕሬዚዳንት አልሲሲ መንግሥታቸው ከኳታር ጋር ዕርቅ ማውረዱንና ለዚህም የሳውዲ ዓረቢያ መንግሥት የተጫወተውን ሚና አድንቀዋል።

## ህወሓት የ40 ኛ አመት የዘረኝነት በዓሉን ለማክበር

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የተዘጋጁትን ቆብ ደፍተው እጃቸው በንጹሃን ኢትዮጵያውያን ደም ከተጨማለቁት የስርዓቱ ቁንጮዎች ጋር ፎቶ ተነስተው መታየታቸው አገራችን የደረሰችበትን የሞራል ዝቅጠት ነው የሚያሳብቀው የሚሉት አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያኑ ዘረኛው ህወሀት ያልፋል፤ እነ በረከት፤ ስብሃትና ሌሎቹም ጉጅሌዎች ከነታሪካቸው እስከወዲያኛው ይጠፋሉ፤ አገርና ህዝብ ግን ሁሌም ይኖራል፤ የህዝብ ነኝ እያሉ የሚጮሁ "አርቲስቶች" ከታሪክ ተጠያቂነት ፈጽሞ አያመልጡም ሲሉ ወቀሳቸውን እየሰነዘሩ የሚገኙት ኢትዮጵያውያን ጥቂቶች አለመሆናቸውን ዘጋቢያችን ከተለያዩ ሶሻል ሚዲያዎች ያሰባሰባቸውን አስተያየቶች በማጠናከር ያደረሰን መረጃ ያሳያል።